# “ ይድረስ በየአድራሻው ”

የተከበራችሁ አንባብያን በየደቂቃው በውስጣችን የሚንኮባቸውን የሐገራችንንና የሕዝባችን አበሳ እንቅልፍና እረፍት የሚነሳ ህመም ሆነና በብዕርና ወረቀት ተመጥኖ አያልቅም።

ይኸ እጅግ እየከፋ የሚሄድ መከራ፣ ዛሬ ሃይልና ስልጣን በእጃቸው ያስገቡትን ጨምሮ ይዋል ይደር እንጂ የሁሉንም ቤት የሚያንኳኳ ነውና፤ሁሉም አርቆና አጢኖ እንዲያስብ፣እንዲተገብር አርዕስቱ እንድሚጠቁመው በሚከተሉት አምስት ንዑስ-ርዕሦች በየአድራሻው አቅርቢያለሁ።

**ንዑስ ርዕስ** | **ገጽ**


1) ይድረስ ለወያኔ/ኢሕአደግ/ተለጣፊዎችና እንዲሁም ለአጋዚ ጦር፦ 1
2) ይድረስ ለኢትዮጵያ መለዮ ለባሾ፦ 7
3) ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነትና አርነት ተዋጊ ሃይሎች፦ 10
4) ይድረስ በውጭ ሀገር ለምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን፦ 13
5) ይድረስ በእስር ላይ ለምትገኙ የሕዝብ መሪዎች፣የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና፣ ጋዜጠኞች፣ እንዲሁም ሲቪል ዜጎች፦ 18


---------------------------------------- // ----------------------------------------

## 1) ይድረስ ለወያኔ/ኢሕአደግ/ተለጣፊዎችና እንዲሁም ለአጋዚ ጦር፦

- በዚች ትንሽ የይድረስ መጣጥፌ በያላችሁበት የምገልጸው እንደተዋጣለት የቋንቋ ሊቅ በአንዳች ቅኔያዊ ምትሀትና ክህሎት የሚቃትተውን አእምሮአችሁን ጨምዶ በሚቂይድ ትረካ ላዝናናቹሁ ወይም ናፍቆቴን ልገልጽላቹሁም አይደለም።

ወይም ደግሞ፣

- በየአቅጣጫው እያደነና እያሳደደ የሚዋትተውን፣ እየፈራ የሚበረግገውን መንፈሳችሁንና ቀልባችሁን ሰቅዞ በምያንጠልጥል ድርሰት ላዘናጋችሁም አይደለም።

ብሎም፣

- ጨክኖ የተበተውን የልባችሁን እዝነ ልቦና ሰብሮ አንጀታችሁን እንዲያራራ ተማፅኖና ደጅ ጥናታዊ ልመናም አይደለም።

- አለዚያም ከዘምናችን የፖለቲካ ሊቃውንት ጥልቅ ጥናት ተዳጉሦ፣ የመፃህፍት መንጋና አንቀጽ አጣቅሶ የሚቸረቸር ምናባዊ ዲስኩርም አይደለም።

- ወይንም ደግሞ ከፈጣሪ የተላከ ነኝ ባይ አንዳች መንፈሳዊና ባህታዊ ራዕይ፣ 'የሰምንተኛው ሺ.ህ' ዐይነት ትንቢትና ስብከትም አይደለም።

ይልቁንም እናንተን (ወያኔዎችን) ጨምሮ በሰባ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያን አእምሮ፤እንደበትና ሁለመና ሌት ተቀን የሚብላላውን ፍጥጥ ያለ አብይ ጉዳይ በየጎዳናው ወጭ ወራጁ፣ የሚነገረውን የውስጣችንን እውነቱን በእራቁቱ አፍረጥርጠን ነው።

ለቀባሪ ማርዳት እንዳይሆን የምጠቃቅሰው አንኳር አንኳሩን ብቻ ነው።

አገራችን ኢትዩጵያ፣ ሕዝቧ፣ ታሪኳ፣ሕገመንግሥቷ፣ኢኮኖሚዋ አንድነቷ እንዲሁም የሕዝቧ ሰላምና ህልውና በከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቋል።

ምናልባት ለጊዜው በዙሪያችሁ በሚያጅቧቹሁ እስከ አፍንጫ ባስታጠቃቹሃቸው አጋዘ ነፍሰ ገዳዮች ታጅባችሁ የድንጋይ ወይም የብረት አጥሩ ተሸሽጋቹህ ቅጽበታዊ ምቾታችሁ የምድረ ገነት ሊመስላችሁ ይሆናል።

በቀውጢው ሰሞን ግን ሁሉም የውሃ ሽታ ይሆናል፤ የሕዝብን ቁጣ የሚመክት አንዳች ኃይል እንደሌለ ሺ. ጊዜ ተመስክሯል፡ የብረት አጥሩ፤ ግድግዳው እንደ አገዳ እና ጭራሮ ሳር ያህል ሳይመክት፡ ይደረምሳል፡ ይጋያል።

የአጫፋሪዎች ጡርንባ፤ አድንቁሯቹሁ ከሆነ አልሰማ ያላችሁ ወይንም፤በሆድ አደሮቹ ግርግርና ዳንኪራ የተነሳው አቧራ እይታችሁን ጋርዶት ከሆነ ትቢያው በቅጽበት ሲሰክንና ንፋስ ሲበትነው የማትወጡት ተራራ ከፊታችሁ አፍጦ ተደቀኗል።

እልፍ ጊዜ በልጠዋቹህ በአደባባይ የረቷችሁን እውነተኛ የሕዝብ ተመራጮች፣የቅንጅት ፓርቲ መሪዎችን፣እንጋፋ የሰበዓዊ መብት ተሟጋቾችን፣ በሞያ ብቃታቸውና በሕዝብ ታማኝ ሆነው ለሀቅ የቆሞትን ጋዜጠኞች ጭምር፣ በሞትና የስቅላት፤የዕድሜ ልክ ይፍታ የፈጠራ ወንጀል አበሳቸውን አብዝታችሁ አንጋግታችሁ በእሥር ቤት ማገታችሁ፣ ቁጥር ስፍር የሌለውን ሰላማዊ ዜጋ አግዛችሁ በየጠረፍ ማጎሪአችሁ ለስቃይ መዳረጋችሁ፤ እልካችሁን ጥላቻችሁን የቀን ጎልበታችሁን ስላሳያችሁ ድል ያደረጋችሁ፤ ሰላም ያገኛችሁ መስሏችሁ ይሆናል።

ይህ ደግሞ ትልቁና ከመጠን ያለፈው ስህተታችሁና ዓለም ያወቀው እንድያውም የመጥፊያችሁ ዋነኛው መንስዔ ነው።
እንደናንተማ፡ለራሳችሁ እንድያመች በውስጥም በውጭም ያሉ አጃቢዎቻችሁንና የነፍስ አባቶቻችሁን ምርቃትና በረከት ለማላበስ ለይስሙላ በደገሳችሁት የምርጫ መድረክ

ላይ የደቀናችሁት ወጥመድ ሁሉ ተበጣጥሶ በራሳችሁ ሚዳ በመዲናችን በአዲስ አበባ 23 በዜሮ ስትዘረሩ በሌላውም የመላ ሀገሪቱ ምርጫ ውጤት ተመሣሳይ መሆኑን ስትረዱ ታርክ የማይምረው ውንብድናና ወንጀል በእንግዶቻቹህ ፊት ፈጽማችሃል። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ብስለቱን፤ እውቀቱን ለዲሞክራሲ ዝግጅነቱን ቁርጠ አረጋግጠላቹሃል። በክብር ብትለቁ ትንሽም የሰራችሁት ደግ የተባለ ሥራ ሁሉ በሚሎን ይባዛላቹህ ነበር።

ዳሩ ግን ለብቻው የደላው የናንተ ኅሊናና ከርሥ በምቾት ተኝቶ ባለበት ቀሞ ያንቀላፋ ኖሯል፡ ለዚህም በንቀታችሁ አለዚያም በግምታችሁ ዝቅተኝነት ይመርጠናል ብላችሁም ሳትሞኙ አልቀራችሁም።

ይሁና ሁለንተናው ለዘመናት በማያቋርጥ ፈተና ተጥምዶ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀሊና ግን ከምንጊዜም የበለጠ ነቅቶ ይገኛል፡ በዓመታት ቀድሚችሁ አልፏልም።

አሁን ደግሞ በርሱ፣ በልጆቹና በመሪዎቹ ላይ የውሰዳችሁትን፣ የምትፈጽሙት ታላቅ ሴራ እጅግ አበሳጭቶታል፣ ለትዕግስቱና ለአስተዋይነቱ መጨረሻ የለውምና በአጠመዳችሁለት ወጥመድ ተንጋግቶ ገብቶ በሺዎች ደመ-ከልብ ስላልሆነላችሁ የተረታ፤ የተሸነፈና እንዲያውም ተቀብሏቹህ የተቀመጠ መስሏችሁ ይሆናል።

ዳሩ ግን እንኳንስ በአገር ውስጥ በየቀኑ አይኑ ስንት ነገር እያሳየው፣ የሚመስከረው ቀርቶ በውጭ አገር በግንቦት ወር 1997 ዓም በኢትዪጵያ ምርጫ እንኳ ስለመካሄዱ አስትባቅቶ ያልሰማው በየዕለት ተግባሩ የሚጣደፈው ባተሌ ኢትዪጵያዊ ዛሬ በአደባባይና በጠራራ ጸሃይ በፈጸማችሁት ግፍና በደል ያስነሳው የሰደድ እሳት እጅጉን አቃጥሎታል፤አንገብግባታል፡ በጠለቀ አይነቁራኛው ውስጥ አስገብቷቹሃል።

ይህ በየጊዜው እየሰፋ የሚሄደው የትግል ቋያ በመላው ዓለም ተቀጣጥሏል፡ ከደቡብ አፍረቃ እስከ እስካንዲንቪያን፣ ከአውስትራሊያ እስከ ሰሜን አሚርካ፡ ከላቲን አሜሪካ እስከ ሩቅ ምስራቅ ተጧጡፏል። የማይበርደው ይህ የትግል ነበልባል የወገኖችን ገዳይ የእሳት እራት የሚያድርግ እሳተ ገሞራ ነው፣ የሚፈነዳውም በርሱ ጊዜና ሰዓት ሳታስቡት ይሆናል።

በዲፕሎማሲውም መስመር እንደ ነፍስ አባት የምትመጻደቁባቸውን አንዳንድ የምዕራባዊያን መንግሥታት ለመረጣቸው፥ ሕዝብ ሰቆቃውን በማጋለጥና በማስተማር መሪዎቻቸው ከእንዲህ አይነቱ መንግሥት ጋር ያለውን ትብብር በቁጣ አውግዘዋል፡ በጥቅም ከናንት የወገኑትም እንደ እነ አሜሪካን ጨምሮ ፓሊሲያቸውን እያስቀየረና ለኢትዪጵያ ሕዝብ ድልና ድጋፍ እያስመገበ ይገኛል።፡ይኸ ለናንተም የተሰወረ ራስ ምታት ባይሆንም እንደልማዳችሁ በተጠናወታችሁ የንቃት መንፈስ ደንዝዛችሁ ታሸልቡና በዱብዕዳ ትነቁ ይሆናል።

ዛሬ ኢትዮጵያዊ ሁለመናውን መስዋዕት ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል፡ የጠላቶቹንም አቅምና ማንነት ከምንጊዜም በበለጠ ጠንቅቆ አውቋል፡ እናንተ በበኩላችሁ ከሰብአዊ የተፈጠራችሁ ሰዎች አርቃችሁ ማሰብ ከጀመራችሁ እርቀ ሰላም አሁንም የተቀደሰውና ተቀዳሚው መንገድ ስለሆነ፡ ባሁኑ ጊዜ ለማንኛውም ፡ኳሷ ያለችው በናንተ ሜዳ ክልል ነው”

አውቃችሁም ይሁን ሳታውቁ የገባችሁበት የዕልክ፤የጥላቻ የበቀልና የቂም ሰይጣናዊ መንፈስ አደንቁሮና፤አውሮ አሁንም እየጋለባችሁ ከፊት ለፊት የተደቀነው የመከራ ገደል አልታያችሁ ብሎ በዚሁ አደገኛ መንገድ ከቀጠላችሁ አይናችሁ አፍጦ እያዩ በገደሉ የመውደቁ ጉዳይ ምርጫችሁ ሳይሆን እጣ ፈንታችሁ ይሆናል።

እስካሁን በፈጸማችሁት በደል የኢትዩጵያ ሕዝብ አይምረንም፤ይቅር አይለንም፤ ከናንተ አይደራደርምና የመጣው ይምጣ የሚል የሞኝነት አባዜ ተጠናውቷችሁ ይሆናል፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እጅግ ታጋሽ፤ ሆደ-ሰፊ፤ አስተዋይ፤ ይቅርባይና መሃሪ ነው። በኀይማኖቱ፤ በእምነቱ በቃል ኪዳኑ ጸንቶ የሚኖር በብዙ ሺህ ዘመን ታሪኩ ብዙ ያሳለፈ ጠንካራ፤ጀግናና ኩሩ ሕዝብ ነው።

በባህላችን መታረቅ፤ መሸማገል መወቃቀስ መካካስ የኖረ ባህሉና ታሪኩ ነው፦ በመሆኑም እናት አባቱን ወንድም እህቱን ልጅና ሚስቱን ከገደለ ደመኛው ተሸማግሎና ታርቆ በሰላም አብሮ ቃሉን ጠብቆ የሚኖር ይቅር ባይ ስለመሆኑ ሌላ ምን ዋቢ አያስፈልገውም።

ታዲያ ይሕ አይነቱ እርቀ-ሰላም የማውረድ መንፈስ ከአንገት በላይ ወይም ለይስሙላ የሚደረግ አይደለም። እጅግ ተጨንቃቹሁ ተጠባቹሁ ከውስጣችሁ አምጣችሁ አስባችሁ፣ ልምድ ባህሪያችሁን ለውጣችሁ ተበድሎ የተቀየመውን ሕዝብ በምህረት ጥያቄያችሁና ይቅርታችሁ ልቡን ስትማርኩት ነው።

በባህላችን ትቢት ወይም ጥጋብ የነሸጠው ጉልበተኛ አንድን ደካማ ሰበብ ፈልጎ መበድሉ የራሱ ኅሊና ውሎ አድሮ ከልብ ሲያስፀፅተው ወይንም በሽማግሌ ወቀሳ ልቡ በአድራጎቱ ሲቆረቆር ድንጋይ ተሸክሞ የበድለውን ደካማ እግር ስር ወድቆ ይቅርታ ይማጸናል፡አድራጎቱ የተበዳይን ሰብአዊና እዝነ ልቦና የሚያራራ ስለሆነ ሸክሙን ከትከሻው ያነሳና በመተቃቀፍ እርቀ ሰላም ያወርዳሉ። ይህንን የመሰለ የተቃቃረን ልብ የሚያቆራኝ ባህል በማንኛውም ሀገርና ሕገ-መንግሥት የሚፃፍ ሕገ ደንብ በላይ የሚገዛ የሚያስተዳድር ወደር የማይገኝለት አንድ የምንኮራበት ለውጩ ዓለም ማስተማር ያለብን የጥንት የሰውል ልጅ ጽኑ ሞራልዊና ህጋዊ ምግባር ነው።

ስለዚህ ይህንን በመሳሰሉት ባህሎቻችንና የተላያዩ የእምነትና የኃይማኖት መሪዎችን የሀገር ሽማግሌዎችን በማሳተፍ በጊዜያዊ ጥቅም ብቻ በተመሰረተ እጃቸውን ለማስገባት የሚሹትን የውጭ ጣልቃገብ በማስወገድ ሀገር በቀል የሆነ እውነተኛ ሀገራዊ እርቀ ሰላም ለመደራደር አሁንም የወያኔ/ኢ.ሕአደግ ዕድሉ በእጁ ላይ ነው።

አንጋግቶ እስር ቤት ያጎራቹሃቸውን የቅንጅት ፓርቲ መሪዎች፣የሕዝብ ተመራጮች፣ጋዜጠኞች ሁሉንም የህሊና እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈቶ፤ ለልጅ ልጆቻን ይኸንን ቁርሾና መዘዘኛ ጦስ ከማውረስ እኛው እንፍታው ብሎ ለእውነተኛ ሀገራዊና ሕዝባዊ እርቀ ሰላም እንሸማገል እንመካከር እንወያይ ብትሉ በአገራችን ማዕዘናትና አድባራት ሰዎችም መላዕክትም በእልልታ የሚቀበሉት መንፈሳዊ አዋጅ በሆነ ነበር።

የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምንም ነገር ባይተውር ሳይሆን በግምባር ቢመክር፤ ቢዘክር በትውልድ የመተዳደኑ የመጠፋፋቱ የመሰደዱ የመከራ ሰንሰለት ይቆረጥ ነበር።

እርቀ ሰላምና ይቅርታ ሁሉንም የሚረታ ከጡንቻ እልፋ ጊዜ የሚከነዳ መንፈሳዊ ኃይል ነውና። በዚህም ነው ቂም በቀልን፤ፍርጃን ሳይሆን ይቅርታና መቻቻልን የመረጡ ጥቂት መሪዎች ዝናቸው በሀገራቸው ብቻ ሳይወሰን በአለማችችን ዙሪያ የሁሉን የሰው ዘር ልብ ማርከው የአሸነፉት፤ ጠላቶቻቸውን ሳይቀር በልጠው የረቱት። የአንድ ሀገርና የሕዝብ መሪ በእርግጥም በታድሎም ይሁን በእውቀት በልምድ ለዚህ አይነት የላቀ ስነ ልቦና  የተካነ መሆን የሚገባው።

ለምሣሌ፡ የደቡብ አፍሪቃ መሪ የነበሩት ኔልሰን ማንዴላ የሕዝባቸውን ነጻነት ለማቀዳጀት በአደረጉት ትግል በጊዘው በነበረው የአፓርታይድ መንግሥት በግፋ ታስረው አብዛኛውን ህይዎታቸውን በአንዲት ጠባብ ክፍል ፈጅተው መስዋትነት የከፈሉለት የጸነሱት ትግል ድል አድርጎ በአሳሪውቻቸው ፊት ለመሪነት ሲበቁ የተከተሉት የፍጹም መቻቻልና አብሮ በሰላም የመኖር ፓሊሲ፤ ጸብን ጥላቻን ቂም በቀልን አርቀው ከራሳቸው በምሳሌነት አስወግደው በማስየታቸው ሀገራቸው ሁሉንም ዜጎች በሚያሳትፍ የእድገትና የሰላም ጎዳና ቀይሰዋል። በዚህም የተባረከ የመሪነት ጥበባቸውና የተመዘነ ትክክለኛ ሰውነታቸው በዘመናችን መሪዎች ወደር የማይገኝላችው በሰው ልጅ የፖለቲካ ህይዎት ውስጥ ሁሌ የሚዘከሩ የዘመናችን ታላቅ ሰው ለመሆን በቅተዋል።

ለወያኔ መንግሥት ሀገራዊና ሕዝባዊ እርቅ ለመፈጸም ከፈለገ በሰከነ ልቦናና ኅሊና ጠልቆ ያስብ ዘንድ ካሁኑ ግድያው እሥራቱን ማቆም አለበት። ይኸንን ለመተግበር ካሃዲዎችን ነፍሶ ገዳዮች ነቅቶ መጠበቅ አለበት። ከሃዲዎች ነፍሰ በላዎች ፀሃይ እንድትወጣ አይፈልጉም ሰይጣናዊ ተግባራቸውና ምግባራቸው የሚፋፋው በጨለማውና፤ በግርግሩ ነውና።

እናንተ በዚህ የመጨረሻ ሰዓት በእጃችሁ ያለውን ዕድል ተጠቅማችሁ እርቀ ሰላም ለመፍጠርና የነገና የተነገ ወዲያ ኢትዬጵያ የፓለቲካ ኅይዎት አካልም ለመሆን ከዳዳችሁ በዓለም ዙሪያ እንደታዬት የተፋጠኑ ታሪካዊ የለውጥ ክንዋኔዎች ባልጠበቃችሁት ሁኔታ ጉድ መሆናቹህ አይቀሬ ነው። ውርደቱ፤ አወዳደቁ፤ ደም-አጥንቱን ሰብሮ ለትውልድ የሚዘልቅ አንገት የሚያስደፋን ካባ ማጥለቁ ምርጫችሁ ሳይሆን ግዴታችሁ ይሆናል።

እጅግ የሚገርመው ደግሞ የጉዳዪ ባለቤት የሆነውን፤ እንወልድሃለን እንዘመድሃለን ብላችሁ ከእናቱ ተፈናጥችሁ የምትጋልቡት የኢትዬጵያ ሕዝብ በቃኝ ሲል ምሬቱን ድካሙን አልሰማ ብላችሁ ዛሬ እናንተ ይበልጥ የሚያስጨንቃችሁና የሚያስጠብባችሁ፥ አነብዳችሁ ጭራ የምትቆሎላቸው እንደ መሳሪያ ለሚጠቀምቧችሁ አንዳንድ ኃያላን መንግሥታትና ወኪሎቻቸው ነው።

ለምሳሌ፥ አሜሪካ መንግሥት እናንተና መላው የኢትዬጵያ ህዝብ በሚያውቀው ጊዚያዊና ‘የወረት ፍቅር’ ከንፋችሁ ለባዕዳን በማደር የቤታችሁን የጓዳችሁን ገመና መክዳታችሁ ነው። ይሁንና አሜሪካ በአለም የውጭ ፓለቲካ ታርኳ እንደምናውቀው በተላይ እንደኛ ድሃና የዕድሜ ዘመኑ በአጭር ከሚቀረጥ አስተዳደር ጋር የሚኖራቸው ቁርኝት እንደ አየር በአየር ንግድ አለታዊ ነው። ‘አሜሪካ ቋሚ ወዳጅም ጠላትም ኖሯት አያውቅም’ እንደሚባለው። በጉልበት አፍናችሁት የታመቀው የሕዝብ ቁጣ ቢገነፋል፤ የሀገራችን ጸጥታ ቢታወክ በ24 ሰዓት ዜኅቻቸውን አጥድፈው ከማስወጣት በስተቀር እናንተን እራሳችሁ የጫራችሁት እሳት ነውና ይሙቃችሁ፤ለብልቦ አመድ ያድርጋችሁ ባዪች ናችው። ስለዚህ ሞትን ሞቶ ማየት ተመልሶ የሚመስክሩለትና የሚማሩበት ገጠመኝ አይደለምና ሞትን፤ እልቂትን ለመቅረፍ በቁርጥ መወሰን አሁን ነው።

እስኪ በቅድሚያ የራሳችሁን፤ የወገኖቻችሁን ኅይዎት፤ከዚያም የሀገራችሁን፥ የታሪካችሁን ደህንነት ለመታደግ ስትሉ ለዚህ ትልቅ ጉዳይ ብላችሁ እልካችሁን ትቢታችሁን ዋጡና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይቅር ተባባሉ።
ግፋና በደሉን ሕዝብና አምላክ በእጅጉ ያቀሉላቹሃል።

## 2) ይድረስ ለኢትዩጵያ መለዮ ለባሽ

ከድሃው ወገንህ አብራክ ወጥተህ በሀገርህ በባንድራዋ በሕዝቧና በሕግ-መንግሥቷ ስም ቃለ-መሃላ የፈጸምክ እውነተኛው የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ሆይ! በሰላማዊ ወገንህ ላይ በየጊዜው የሚፈጸመው አረመኔያዊ ግፋና በደል ግዞት፤ግድያና እሥራት የሚከናውነው በጣም በጠባብ ጐጠኞች ሚስጥራዊ የገዳይ ስኳድና አዛዦቻቸው በመሆኑ ስምህንና መለዮህን በወገንህ ደም ሲያጎድፉት ሙሉ እውነቱን እንድትሰማና እንድታውቅ ወያኔ አይፈቀድልህም።

ለዚህም በየደረጃው ከቡድን መሪ ጀምሮ እስክ ከፍተኛ መኮንኖችና ጄነራሎች ለዚሁ ሴራ በጎጥ የወገኑ ቡድኖች በሰንሰለት የተኮለኮሉበት ስለሆነ ያለብህ ጫናና ቁጥጥር የወገንህን ብሶት እንዳታውቅ የተዘረጋው ጥቁር መጋረጃ እጥፍ ድርብ መሆኑን ወገንህ ይረዳል።

ከዚ ጋር በተያያዘ ከናፋቂ በተሰቦች እንኳ የሚላክ ደብዳቤ ሳይቀር ተከፍቶ እየተነበበና ‘ግምገማ ወይንም ሳንሱር’ እየተደረገ የሚድርስባቸውን እንግልት የሚገልጽ ካለ ተቀዶ ይጣላል። በሌላ በኩል እውነቱን የሚጠቁሙ ጋዜጦችን እንድታነብ ከወያኔ ቁጥጥር ውጭ ያሉትን ገለልተኛና ትክክለኛ የሕዝቡን አበሳ የሚያጋልጡ የሬዲዮ ጣቢያዎችን እንድታዳምጥ እንኳ አይፈቅዱልህም።

እርስ በእርስ በሀገርህ የፓለቲካ ጉዳይ እንድትወያይ ነፃነት የለህም።አለዚያም በወገንህ ላይ በሚፈጸመው ግፍና በደል እንድድትጠይቅ አይፈቀድም፣ ለዚህም እኩይ ተግባራቸው ሲሉ በየሰበቡ ምድብህን፤ ክፍልህን፤ ጓድህን በየጌዜው እንዳሻቸው ይበውዙታል።

አፈትልኮ በደረሰ እውነት ተቆጥተው ጥያቄ ያነሱ ባልደረቦችህ በሚስጥር ተለቅመው ታሰረዋል፤ እንደ ጠላትም ታይተው ተገድለዋል፤አለዚያም በባዶ እጃቸውን ተባረዋል።

ወያኔና ሻቢያ ንፋስ አይገባበትም ብለው የከነፋበት የአፍላ ፍቅር ወረቱ ቀዝቅዞ ሲፋቱ በንዋይ ክፍፍላቸውና በጥቅማቸው ጥጋብና ቅናት ባስነሱት አምባጓሮ አንተን ማግደው ከአርባ ሺህ በላይ የሚሆን የሞያ ባልደረባህን ደመ-ከልብ አድርገውት ቀርተዋል። የወያኔው ደንታ ቢስ አለቃ የአሳበቡበትን የአገር ጉዳይ ከመጤፋ ሳይቆጥሩ በፊርማቸው በአለም ሽማግሌዎች ፊት የሃገርህን መሬት አሳልፈው ሰጥተዋል። ይህ ታሪክና ትውልድ ይቅር የምይለው የክህደት ሴራ ገና ብዙ ደም የሚያፋስስ የሚያገርሽ ቁርሾ ለመሆኑ አሁንም ምንጊዜም በላያችን ጠርነት እንዣቦ ይገኛል።

አሁንም የወያኔዎች ሰይጣናዊ ተልዕኮና እኩይ ተግባርን ሕዝቡ ይበልጥ እየተገነዘበ በመጣ ቁጥር በሕጋዊ መንገድ ሲፈታተናቸውና ሲጠይቃቸው ከራሱ አብራክ የወጣውን

መለዮ ለባሹን እንደ ግል ዘበኛቸው በመቁጠር ወገንህን በሀገራችን መዲና፤ሕጻናትና እናቶችን፤ወጣትና አዛውንቶችን ሳትለይ በመደዳው እንድትጨፈጭፍ ቀጭን ትዕዛዝ ሲሰጡህ ቆይተዋል።

ከዚህ የበለጠና የከፋ እልቂት እንድትፈጽም ቢያንገራግሩብህም በግል ከሚቀልቧቸው ተናካሽ የአጋዚ ውሾቻቸው በስተቀር አብዛኛው የጦር ባልደረባ ከዚህ ታቅቦ በትዕግሥት መቆየታቸውን ወገንህ ይኸንን ሚስጥር በየጊዜው ይሰማል።

እንደ ፍጹም አረመኔያዊ የወያኔ መሪዎች ምኞትማ ቢሆን ኖሮ የመዲናችንን ሕዝብና በምርጫ የሰዋቸውን ክልሎችና በሕዝብ ድምፅ የረቷቸውን ተመራጮች ሁሉ በቅጽበት ጨርሰው ከመፍጀት አይታቀቡም ነበር።

አሁንም እነዚህ ደምና ንዋይ ያሰከራቸው ከሃዲዎች ከባዕዳን ጋር በአገራችንና በሕዝባችን፡በታሪካችን፡በባሕላችን ከምንጊዜም የበለጠ አሲረዋል።

ሕዝቡ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ድምጹ እንዲከበር ሲጠይቅ የሰጡት ምላሽ በአደባባይና በጠራራው የጥይት እሩምታ በማውረድ ነው። ቤት ለቤት ዙረው፤ጓዳ አሰሰው በተለይ በዘር ላይ ባነጻጸረ ጥላቻና ቂማቸው በዚህ የመጨረሻ ሰዓታቸው ወገኖችህን እንደ እቃ አነባብረው በካሚዎን እየጫኑ በየጠረፉና፤ በየዋሻው በማጎር የግርፋትና የሞት ሰለባ አርገውታል። በሁለተኛው የአለም ጦርነት ዘመን የጀርመን የናዚ መንግሥት በእስራኤላዊያን ዘሮች ከተፈጸመው የመንጋ ግዞት ወዲህ በዓለማችን በድጋሚ በዚህ የስልጣኔ ዘመን በኛው ሀገር ኢትዪዮጵያ እየተፈጸም ይገኛል።

በመሁኑም ግምቱ ወደ መቶ ሺህ የሚጥጋ ሰላማዊ ህዝብ በወታደር ካሚውን እየተጫነ፡በዴዴሳ፤በሁርሶ;በሸዋ ሮቢት፡ በብር ሸለቆ በዝዋይና በሌሎችም የመግረፊያና የመግደያ ጣቢያዎች ታጉሯል። ሕይዎቱን በአስቃቂው ገዳይ ደዌ ለመበከል ባላቸው ሰይጣናዊ ደባ ያገቱትን ህዝብ አስገድደው በአንድ ምላጭ እስኪዶዱም ድረስ በርካታ ሰው አድምተው እየላጩ በቁሙ ሞት ፈርደውበታል። ይኸንን የሰሙ በውጭ የሚገኙ ወገኖችህ ለዓለም ሕዝብና መሪዎች አቤቱታ በየጊዜው ያቀርባሉ። በአለንበት ዘመን የሰው ልጅ ከኋላቀር ዘመን የበድልና የእልቂት ስህተቱ ተምሮ የሰው ልጅን ሰብዓዊ መብቶች ለማስከበር አባል አገሮችንና መንግስታቶችን በበላይነት የሚዳኝ፡በተባበሩት መንግስታት ስም የተዋቀረና የተመሰረተ አካል ቢኖርም፡በውስጠ ታዋቂነት በሓያልን አገራት የበላይ አዛዥነት የሚመራ ከባድ ተጽኖ ያለበት ድርጅት በመሆኑና፡እኒሁ ሃያላን መንትስታት በድንበር ዘለል ፓሊሲያቸው ለጥቅማቸው በሚያቋቁሟቸው እንደ ኢትዪጵያው ባሉ የወያኔ ዓይነት የአሻንጉልትና የባንዳ መንግስታት ላይ ጠንከር ያለ አቋም እንዳይወሰድ ደንቀራ መሆናቸውን በአምባሳድሮቻቸው እስከ ግለሰብ የህግ ጉዳይ፤ሕዝብ በመረጠው ፓርቲ ቅንጅት ስም በካሃዲዎች የሚመራ ውራጅ ፓርቲ

እስከማቋቋም ጣልቃ እየገቡ እንዳሻቸው በውስጥ ጉዳይችን ላይ ሰፈተፍቱ እንመሰክራለን።

በሌላ በኩል የአውሮፓው የሕብረት መንግስታት ፓርላማና ሌሎችም በአለም ዙርይ ያሉ በርካታ መንግስታት ሀገርና ሕዝብ ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በየጊዜው በሚያድርጉት የሚያቀርጥ የማጋለጥና የአቢቱታ እንቅስቅሴ መንግስታቱ ምላሽ የመስጠት ግዴታ ሆኖባቸዋል። ስለልሆነም አንዳንድ አበረታች ጅምሮችና ውሳኔዎች የኢትዩጵያን ሰፊ ሕዝብ የትግል አጋርነትና ድጋፍ በሚያረጋግጡ መልኩ ውሳኔዎች እየተላለፉ ነቸው።

ፍጹም ታጋሽ የሆነው ኢትዩጵያዊ ወገንህ ለአሥራ አራት ዓመታት መከራና ስቃዩን ተሸክሞ ከቀዬ በሑዋላ በተካንደው ብሔራዊ ምርጫ በከፍተኛ ቁጥር ወጥቶ የወያኔን ቡድን በምርጫ ካርዱ ሽሯል። በምትካቸው እውነተኛ ሀገራዊና ሕዝባዊ ራዕይ ይዘው ሁልንም ኢትዩጵያዊን መብትና ነፃነት በሚያስከብርና በሚወክል አጀንዳ የተነሱትን ቅንጅትንና ሕብረትን መርጧል።

ይሁን እንጅ እብሪተኛው ወያኔ የዘረጋው ሴራ እንደለመደው አጥምዶ ሳይዝለት ሲቀር በሕዝቡ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና በመላው ኢትዩጵያ ሕዝብ ነጻነትና ኅልውና ላይ ላልተውሰነ ጊዜ በሚል ማዕቀብ ጥሏል። የሕዝቡን ድምጽ በጉልበት ሰርቋል። ብርቅ ድንቅ የሆኑትን የነጻነትና የሰላም ታጋዮች፤ሙሁራኖች፤ የሕዝብ መሪዎች አዋክቦ በእስር በት በማሰቃየት ላይ ይገኛል።

በዚህ አድራጎቱ የኢትዩጵያን ሕዝብና ወዳጆቿን ከምንጊዜውም በበለጠ አስቆጥቷል፣ ወያኔ ይህ አድርጎቱ ለዓመታት በሃሰትና በድለላ ዘዴው ተክኖ፣ ድጎማ የሚያቀናበትና የሚቸረቸርበት ፕሮፓጋንዳ ተጋልጠ የልመና ቁናው ባዶ ሆናል፣ የውጭ ፓለቲካዎም ከፍተኛ ኪሳራ ደርሶበታል።

የአውሮፓ ሕብረት መንግሥታት በቀጥታ የሚሰጡትን እርዳታ አቁመዋል።በቅርቡ የወያኔ ነፍስ ገዳይ ቡድንና አዛዦቻቸውን፤ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትን ጨምሮ የጉዞ ማዕቀብና ዘርፈው በዓለም ዙርያ ባጠራቀሟቸው የባንክ ሂሳቦቻቸውን እንዳያንቀሳቅሱ የሚያግድ ህግ ለማውጣት በዝግጅት ላይ ሲሆኑ ሌሎችም በርካታ መንግስታት ለወያኔ የጡት አባት የሆነችውን አሜርካንም ጨምሮ በሕዝቧና በበርካታ ለኢትዩጵያ ህዝብ ጎን በቆሙ እንደራሲዎች ግፊት የጠበቀ እርምጃ ለመውሰድ ተገዳለች። ውሎ ስያድር የወያኔ ቡድን የማይወጣበት አጣብቂኝና መቀመቅ ላይ ይወድቃል።

ይሁን እንጅ የኢትዩጵያ ሕዝብ የተፈጠርውን አጋጣሚ ተጠቅሞ ለበቀል የሚነሳ ሳይሆን ይህ የአንዣበበ መከራ ወያኔን ትንሽ ቆም ብሎ እንዲያስብ ቢያደርገውና

ኢትዮጵያዊያን የዘረጉንትን የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄ እጅ እንዲጨብጥ፤ወደ ምክክር እንዲቀርብ ቅድሚያ የሚሰጠው አሁንም የሰላም ጥሪው ነው።

ነገር ግን ከእልኩና ከትቢቱ፤ ከስህተቱና ከጥፋቱ አልማር ብሎ በዚች ማንቁርቱን ማነቂያ እያጠበበች በመጣች ቀጭን ቀን የእብደትና የውንበዴነት ባህሪው ይብስ አገርሽቶ እርቀ በቆፈረው ጉድጓድ አፋፍ ላይ ሲደርስ አጥፍቶ የማጥፋት ጠሱን በማሰብ ውድ የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ለወገንህ የቁርጥና የክፉ ቀን ደራሽና መድህን ትሆን ዘንድ ካሁኑ ሁሉን በዐይነ ቁራኛና በተጠንቀቅ ነቅተህ እንድትጠባበቅ ቤተሰቦችህና፤ወገኖችህ በአጽንዖት ይማጸኑሃል።

## 3) ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነትና እርነት ተዋጊ ሃይሎች፦

"የበግ ለምድ የለበሰ ጅብ ምንጊዜም ጅብ ነው" አበው እንዳሉት ሆኖ ሳለ እውነታው ወያኔ ተደራርቶ በጥቂት የጡት አባት ምዕራባዊያን አለልኩ የተሰፋለትን 'ሳልቫጅ' የዲሞክራት ቀብና ጃኬት አጥልቆ በደገሰው መርዘኛ ምርጫ ጉድጉድ ሲል ቆየና በሽንፈት ሲዘረር እርቃነ ገመናውን ቀርቷል። የራሱን እውነተኛ የገዳይ የወያኔ መለዮን አጥልቆ ሰላማዊ ኢትዮጵያዊያንን በአደባባይ በመፍጀትና ቁጥር ስፍር የሌለው ሰላማዊ ሕዝብ አግዞ በማሰቃየቱ፤ እውነተኛ የሕዝብ እንደራሲዎችን፣የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን፤ጋዜጠኞችን ለእስር በመዳረጉ ሰቀቃው ለዓለም ህዝብ አልፎ በመጋለጡ ከወንበዴነት/ቴሬሪስትነት ወደ ዲሞክራት በሚል ስም ያዋሱትን እውቅና ሰጭዎችን ጭምር አድርራጉቱ አሽማቋል።

'መልክ ጥፉን በስም ይደግፉ" እንዲሉ የወያኔ መሪዎች በምስራቅ አፍሪቀ ስልጣን ሞጭጨው ከሕዝባቸው ይልቅ ኃይላን መንግስታትን ሙጥኝ ብለው ለባዕዳን ጥቅም ከሚያሽረግዱ የምስራቅ አፍረቃ አቻ መሪዎች ጋር ተዳምረው 'የአፍረቃ የአዲሱ ትውልድ ተራማጅና ዴሞክራት መሪዎች"፣ እየተባሉ ሲሞካሹ ቆይተዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀውና በአሥራ አራት የመከራ ዓመታት ያሳለፈው ገሀድ ግን ይህ በአናሳ ጐጠኞች የዘረኛና ጨካኝ ቡድን የፈጠጠ የዲክታተር ተግባሩን ነው፡ ከፋፍሎ የመግዛት፤ የመግደል፤ የእስራት፤ የስደት፤ ሀገር ቀርሶ የተሸጠበት፤ ጥቂቶቹ በስልጣናቸውና በዘራቸው በጥቂት ዓመታት ሚሌየነር የሆኑበት፡ፍጽም ግፈኛ አስተዳደር መሆኑን ነው።

እጅግ አሳዛኝና አስገራሚ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ በጅግንነቱ ዓለም የሚያውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የምርኳዙን (ሽመሉን)፡ጀንፍ እንኳ ሳይቀር አውልቀው፤ ትጥቁን አስፈትተው ጀሌውን አስቀርተው እነሱ ግን በድሃ ጎኑ ጠሙን እያደረ በከፈልው ግብር

በሽመቱት ዘመናዊ መሳሪያ፣ በታንክና መትረየስ በአደባባይ እያነጣጠሩ ደረት ግንባሩን ይመቱታል።

በጣም ከሚዘገንነው ፍጽም የወያኔ ቡድን ፋሺስታዊ መንፈስ የተጸናውተው ስለመሆኑ የሚያሳየው፡ በአንድ ወቅት በሀገራችን መዲና የአገዛዙ ቁንጮ በቀጥታ በሰጡት ትዕዛዝ የአጋዚ ወታደሮች በተለይ በኰተቤ ክፍለ ከተማና አካባቢዋ ከፍተኛ እልቂት በፈጸሙበት እለት ('ሽብሬ' የምትባለው ወጣት ኢትዮጵያዊ በጥይት በተድፋችበት)፡ምሽት ላይ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የሴት ልጃቸውን የልዕደት በዓል (ፓርቲ) በሸራተን ሆቴል ደግሰው በፌስታ ይቀማጠሉ እንደነበር ነው።

ይህንን በመሰለ አረመኔያዊ ድርጊት ደማቸው የተቀጣ ታዳጊ ወጣቶች ከአስፓልት ዳርቻ በተኮልኮለ ከጠጠር የማይበልጥ ድንጋይ በወረወሩባቸው ገዳይ አጋዚዎች ታንካቸውን እየጋለቡ በመትረየስ ያለምንም ርኅራሄ እያሳደዱ በጥይት ፈጅተዋቸዋል።

ለነገሩማ ወያኔ ከአነሳሱ በሃገራችንና በሕዝባችን ላይ ከውጭ ወራሪዎች በከፋ ማቀዱ የሀገሪቱን ጥንታዊና ብሄራዊ ድርጅቶች አፈራርሷል። ከነዚህም መካከል 'የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊቱን' ሙሉ በሙሉ በትኖ ጀግናው ወታደር ወደ ትውልድ ቀበሌው እንኳ መመለሻ አጥቶ ወይም መተዳደሪ እና መጠሪያ ችግሮች በኒሻኑና በመዳሊያው ምጽዋት እንዲለምናን እንዲዋረድ ተደርጓል።

በአዲስ የተዋቀረው የጦርና የመከላከያ ኃይል ለወያኔ ጥቅም አስቀድመው በዘር ወይንም በጎጥ በወገኑ መኮንኖችና ሃላፊዎች ቁጥጥርና መዳፍ ስር አድርጎ ሃይልን በጥቂቶቹ በሞኖፓል ይዞ በሕዝቡ ትክሻ ላይ እንደ ልቡ ይናጥጣል።

ይህ አድራጎት አስከፍቷችሁ ለረዥም ዓመታት በአስቸጋሪው የአለም ሁናቴ በቆራጥነትና በዓላማ ጽናት አስተዳደሩን ስትዋጉ የቆያቹሁ የነጻነትና አርነት አርበኞች እንዳላችሁ ይታወቃል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ እጅግ በተባባሰው አሰራትና ግድያ ባስከተለው በደል ይበልጥ በተቀናጀ መንፈስና ስልት በሀገራችን ዙሪያ-ገባ የትጥቅ ትግሉን ያጠናከራችሁ የመከራ ቀን ወንድምና እህቶቶቻችን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ

ይሆኖል መስሎት በትዕግስት የቀጠለበት የሰላም ትግል ያስከተለበትን እልቂትና መዘዝ ተገንዝቧል። በዚህ ቀውጢ ሰዓት የማይማረውና የማይመከረው የወያኔ የባለጌው ቡድን በህዝቡ ላይ በሚያደርሰውና በሚቃጠበት እልቂት ፈጥኖ የሚደርስለትና የሚመክት፣ሃይል ቀኝ ክንድ መኖሩ ይበልጥ አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል።

በሰላማዊ መንገድ የተጀመረው ትግል እስከ መጨረሻው የሚቀጥል ቢሆንም አካሄዱ ከመጠን የከፋ መስዋዕትነት እያስከፈለ ከመሆኑም በላይ የወያኔ አጸፋ ፍጽም ጭፍጨፋ በመሆኑ አማራጭ የትግል ዜዴ ወሳኝ ነው።

ለሕዝቡ ሕይዎት አንዳች ደንታ የሌለው አረመኔያዊው ወያኔ እንደ ቅጠል በከንቱ የሚያረግፋቸው የነገ ሀገርና ትውልድ ተረካቢ ወጣቶች እየጨረሰ ነውና ይኸንን የሚታደግ በትጥቅም የሚፈታተነውና ለድርድር የሚያስገድደው የህዝብ ሓይልና ወገን አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በሁለንተናው ሊያገኝ ይገባዋል።

ቆራጥ የሆናችሁ የአርነት ታጋዮች እስካሁን ባድረጋችሁት ትግልና በከፈላችሁት መስዋዕትነት ባስገኛችሁትም ድል ለወገናችሁ በምትሰጡት ተስፋ እጅጉን የተበረታታ ሲሆን የወያኔው ቡድን ግን "ውረዱ እንውረድ" እያለ ለዓመታት በጀሌው ሕዝብ በአሽሙር ሲንበጣረር እንዳልኖረ አሁን ብርክ ይዞታል።

በየዘርፍ ላላችሁ አደራችን ጥቃቅን ልዩነታችሁን ወደ ጎን አድርጋችሁ የሀገርና የነፍስ አድን ተልኳችሁን በጸና ቃልኪዳናችሁ በአንድ ላይ እንድትገሰግሱ ነው።

የነጻነት ጀንበርን ጨፍግጎ የጋረዳት ጉም እየለቀቀ ነውና ሙሉ ብርሃኗን መፈንጠቂያዋ ተቃርቧል።

በዚህ መራራ ትግል መስዋዕት ሆነው ያለፉትንና የሚያልፉትን ሰማዕታት ሕዝባችን ለዘለዓለም ይዘክራቸዋል። የሚወዱትን ሕዝብና ሀገር ለማዳን የከፈሉትና የሚከፍሉት ትልቅና የተቀደሰ መስዋዕትነት ስለሆነ ነፍሳቸውን ጻድቅ ነው፤ገድላቸውም ዘለዓለማዊ ነው።

ይህ አስከፊና ፈታኝ ዘመን የኢትዩጵያ እውነተኛ ወዳጀቿና ጠላቶቿን እንድትለይ አድርጓታል።

በአሁኑ ጊዜ ስለሀገሩና ወገኑ ብሶት በየደቂቃው የማያብሰለስል ዜጋ የለም፤ የመከባበር፤የመፈቃቀርና የአንድነት ትልቅ መንፈስ በኢትዩጵያዊያን ዘንድ እየሰረጸ ስለሆነ የከፋፋዩ የወያኔ ቀን እየጨለመ ነው።።

በሰላም የምትደምቀዋ ጸሀይ ለሁላችንም ታበራለች! ትሞቃለች። በርቱ!

የኢትዩጵያ አምላክ ይጠብቀን!

አሜን!

## 4) ይድረስ በውጭ ሀገር ለምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን፦

*በአጼው ዘመነ መንግሥት፣ በደርግና በቅርቡም በወያኔ የምንወደውን ሀገርና ሕዝብ ትተን በስደት በዓለም ዙሪያ ተበትነን የምንገኝ ኢትዩጵያዊያን ሆይ፣ መንግሥትና የአገዛዝ ሥርዓቶች በየጊዜው ይለዋወጣሉ፣ ነገር ግን ሐገር እና ቅርሷ ለዘለዓለም ተጠብቀው ለትውልድ የሚተላለፉ አደራዎች ናቸው።*

*በአሁኑ ሰዓት ኢትዩጵያ ሀገራችንና ታሪኳን እያፈራረሱ ያሉት ከሃዲዎች ሥር አግራቸውና ቅርንጫፋቸው ከባህር ማዶ የመደረ ነው። ይህንን በያለንበት የዘመናችንን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ግማደሸ ቆርጦ የሚለያይ ለሀገራችን ኢትዩጵያ የሚቆም ከእውነትኛ ልጆቿ ሌላ ምንም ሃይል የላትም፡ የኛ ድሃ ቤተሰቦች በጠራራው ተሰልፈው በመረሸን አለዚያም እንደ ጥንቱ ጨካ ገብተው በመሸፈት ብቻ የሚያቀኑት መከራ አይደልም፡፤ ሴራው አለማቀፋዊ ውንብድና ስለሆነ በምንችለው ሁሉ ቀንደኛ ተዋንያን መንግሥታትን ጨምሮ ማጋለጥና መሞግት ይጠበቅብናል። ይሕንን ለዘመናት እያስቀዘመ የኖረ ኢፍትሃዊ የፖለቲካና ብልሹ አስተዳደራዊ ባህል ተዋግተን ዓለም በፍጥነት እየተፈናጠጠበት ወደሚገኘው ዴሞክራቲክ ጐዳና ሕዝባችንና ሀገራችንን የማሸጋገር አደራና ኃላፊነት አለበን።*

በአገራችን ኢትዩጵያ እንዲሁም በአሕጉራችን በአፍሪቃ የፖለቲካ፤ የሐገርና የሕዝብ አስተዳደር ከረዥም ጊዜ ጀምሮ አሁን እስካልንበት ዘመን ድረስ በአብዛኛው የየሀገሩ ዜጎች በብቃታቸው፤በሕዝባዊ አቋማቸው የተፈተነና የተመሰከረ ልምዳቸው፤ሕዝቡ ፈልጎ በመረጫቸው አይተዳደርም። አብዛኞቹ ይዘቱ እንደ ዘመኑና እንደ ሃገሩ ነባረዊና ታሪካዊ ሁኔታ በቅርጽም በይዘትይም ቢለያይም በአንጻራዊ ተመሣሣይነቱ፡ አንዱ ቡድን ጠብ-መንጃ አንግቶ፤ወግቶ ከበፊታቱ የነበረውን መሪና አስተዳደር በአፈሙዝ ዘርጦ፤በከርሰ መቃብሩ ላይ የሚተካ የየቀኑ ግልበተኞችና በለስ የቀናቸው ሹምሽር ነው።

ይህ ደግሞ የሚያስተውል ኅሊና ላለው ዜጋ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን እውነተኛ ክብርን ውይም እርካታን የማያስገኝ፤የከርሳሞችና የደንታ ቢሶች በሰው ኃይዎት ቁማር መጨዎቻ መድረክ ሆኖ ኖሯል።

በሀገራችን በኢትዩጵያም ሲከናዎን የቆየውም ይኸው ነው፡ በተለይ በታረክ ወደ ኋላ ብዙ ሳንጓዝ የ1966 እ.ኢ..አ ጀምረን ብንመለከት እንኳ በሰፊው አርሶ አደርና ሠራተኛ ምሁራን ብዙሃን ዜጐች በዘመኑ በነበረው አዝጋሚ ለውጥ ብዙ የመከራ ዘመን አስቆዝሞ የገንፈለው ሕዝባዊ ትግል የሚመለክባቸውን የንግሥተ-ነገሥቱን የዘውድ አገዛዝ ሲያንበረክክ አጋጣሚውን ተጥቅሞ የወታደሩ ስብስብ ‘የጊዚይዊ አስተዳደራዊ አስተዳደር ደርግ’ እና በኋላም ‘ኢሠፓ’አኮ’ እያለ ድሉን በሃይል ጠለበና አብዮት በሚል ስያሜ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ አመራው።

በጊዜው ይህ መጥፎ አካሄድ የገባቸው በርካታ የተማሩ ሃይሎች ከዘላቂ የሕዝቡ ጥቅም ወግነውና ተደራጅተው ሞገቱት። ይሁንና ፍጹም አረመኒያዊ በሆነ መንገድ ስልጣን ቀምሶ ያቅመጠመጠው ወታደራዊ ኃይል 'ቀይ ሽበር' በሚል ዘመቻ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የሕዝብ አንጡራ ልጆችን በየአደባባዩና መንገድ ዳርቻው በግፍ ጨፈጨፋቸው።
ይህ መከራ ከከተማ እስከ ገጠር ቤቱን ያላንኳኳበት በተስብ የለም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር እስከ ዳር በልጆቹ ሞት የሃዘን ማቅ አልብሷል።

ሐገራቸውን ወደ ዕድገትና መሻሻል ለማሳደግ ተስፋ የተጣለባቸው የሀገሪቱ የዘመናዊ ትምህርት ተቋዳሾች ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ተቋማት የሚገኙ ምሁራንና ተማሪዎች በዚሁ የዕልቂት ዘመቻ እንደ እሳት እራት በእፍቱ ተጠበሱ።

የተረፉትም ወደ ባዕዳን ሀገራት የሚወዱትን ሀገርና ሕዝብ ጥለው ተሰደዱ፤ በታሪካቸውና በባኅላቸው እንደ አውሮፓዊ ወይም ምዕራባዊ ዜጋ በሀገሩ እንደሚኮራ ልበ ሙሉና ኩሩ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች በሰው ሃገር የሚያመጣውን የሁለተኛ ዜጋ የመሆን፤ የሙብትና የሥራ ዕድል አድሎ በአብዛኛው በሚታዩባቸው ቦታዎች ጭምር በሰው ሀገር የመንገላታት ዕጣ ፈንታና ፈታኝ ወቅት አሳልፈዋል። ይሁን እንጅ ጨዋነት በተሞላበት ሥነ ምግባራቸው፤ታታሪነታቸው፤ለመማርና ለማወቅ ባላቸው ጹኑ ፍላጎት በአጭር ጊዜ ለከፍተኛ ሞያና የሥራ መስክ እራሳቸውን አስከብረው አቅማቸው በፈቀደ ሁሉ ለወገናቸውንና ለሀገራቸው ድጋፍ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ባህልና ታሪካችንን በማስተዋወቅም ረገድ በርካታ አምባሳደሮች ከሚያከናውኑት በላይ አስደናቂ ተግባሮችን በዓለም ዙሪያ እየፈጸሙ በሁለተኛና ሦስተኛ ትውልድና ከዚያም በላይ ደርሷል።

ለማንኛውም ወደ ንዑስ ርዕሱ መንደርደርያ ሃሳብ ማለትም የፓለቲካ ይዘት በአህገራችንና በአሕጉራችን በጥቅሉ ለመቃኘት ባስብኩት ፈር ልመለስና፦

የፓርቲና የፓለቲካ እንቅስቅሴዎች በሀገራችን ከቅርብም ሆነ ከሩቅ መሪር ትዝታዎች ጋር የተቆራኙ በመሆኑ አንድ ሰው ፓለቲካ ሲያስብ አብሮ ' የሬሳ ሳጥኑንም መግዛት አለበት' እስከሚያሰኝ አንድን ዜጋ በሀገሩ፤ በሙብቱና በነጽሳነቱ ወሳኝ ጉዳይ ላይ እንዳይሳተፍ መጥፎ የታሪክ ጠባሳ ጥሎ እንደነበር እንረዳለን።

በሌላ በኩል በዚህ መስክ ምሣሌ ወይም ለትውልድ አርዓያ ለመሆን የበቁ ባለሙያዎች ቀርቶ ወጥነው እንኳ ያለፉ ስመ ጥር አዛውንቶች በዘመናዊ ፓለቲካ የሉንም። ተውኔቱ በአመዛኙ ለጊዚያዊ ጥቅምና ኃይል በሚሳመጡ፤በሚቧጨቁ ስግብግብ ጅቦች የትንቅንቅ መድረክ ሆኖ በመቆየቱ የተዋንያኖች ዕድሜና ጀብዱ ቅጽበታዊ ነው፣በክበር ለጡረታ የበቃና የፓለቲካ ስራውን ለትውልድ በህይዎት ለማስተላለፍ የበቁ የለንም።

በመሆኑም በምሁራንና በአብዛኛው የከፍተኛ ተቋማትም እንዲሁም በሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ በሞከርኩት ልምድና ታሪካችን በመነሳት ፓለቲካዊ ዝንባሌል የሚያመጻድቅ ክህሎትንና የሙያ ዘርፋን የሚገበይበት መስክ እንዳልሆነ በቀጥታም ሆነ በአሽሙር ዓይነት ሲወገዝ ቆይቷል።

ነገር ግን በዘመናዊ ቴክኖሎጅ እና በተለያዩ የትምህርት፤የምርምርና የሞያ መስኮች የተማረ የሰው ሃይል በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የተማሩ ባለሙያዎች አገራችን አፍርታለች። ነገር ግን እኒህ ሙሁራን በሀገራችን ከተሰለፋበት ሙያዊ አስተውጽዖ በስተቀር ፓለቲካው ተሳትፏቸው በጣም የተወሰነ ነው። ይኸም ከላይ በትምህርት ተቋማትና በምሁራን ዘንድ ፓለቲካ ባህልና ተሳትፎ ውስነነት ነው። ይህ ግን ምሁራኑ የፓለቲካዊ ግንዛቤያቸው አነስተኛ ነው እንደማስኘት እንዳይቆጠር እያሳሰብኩ ይልቅስ የምሁራኑን የበሰለ ፓለቲካዊ አመለካከት የሚያካትት ወይም የሚጋብዝ ነጻ መድረክ አልነበረምና ነው።

እንዲይውም በዚህ የደካሞችና የከንቱዎች መሰብሰቢያ ጎራ ተብሎ በሚታማው ፓለቲካ መድረክ ተሰልፈን በአጭሩ እንዳንቀጭ ከማሳሰብ አኳያ ምክርና አደራም ያሉን ምሁራን ነበሩ።

ለምሳሌ፥ ነፍሳቸውን ይማርና በአመርቂ ሙያቸውና ተግባራቸው ዓለም የሚያውቃቸው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘልዓለም የሚወዳቸው በቅርቡም ‘ንቀው በሸሹት’ የደካሞች ጉራ አረመኒያዊ እጅ ሰለባ የሆኑት ታላቁ ኢትዬጵያዊ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ በህክምና ሞያ አሰተምረው ሊያስመርቁ ያበቋችውን እጩ ዶክተሮች በአንድ ወቅት ሲመክሩ፤ ቃላቸውን ባዛባ ወይም ባዛንፍ አምላክ ይቅር ይበለኝና *“.. እናንተ የተጣለባችሁ የሞያ አደራ በጤና እጦት የሚሰቃየውን ወገናችሁን መፈውሰና ጤናውን መንከባከብ፣ ጤነኛና ጠንካራ ዜጋ ማፍራት ስለሆነ ሙሉ ትኩረታችሁ ይኸው ይሁን፣ ድንገት ተሳስታችሁ ፓለቲካ ገብታችሁ እንዳትዘናጉ..”*፣ብለው ነበር ይባላል።

ከትንሽ ዓመታት በሁዋል ግን የወያኔ መንግሥት በጨለማ በእሥር አጉሮ ሲያሰቃያቸው የነበሩት እኒህን ሰመ-ጥር ፕሮፌሰር ለመጠየቅ እድል ያገኘ አንዱ ተማሪያቸው የመከሩትን ያስታውስ ኖሮ *“.. ምነው እኛን እንዳልመከሩ እርሰዎ ለምን ፓለቲካ ውሰጥ ገቡ?..”*፣ቢላቸው፣ *“... አይ ልጄ እኔ የአንድ የደከመ በሽተኛ ወገኔን ህይወት ለማትረፍ ደፋ፤ ቀና ሰል፤ የወያኔ መንግሥት የሺዎችን ጠንካራ ወገኖቻን ህይዎት በአደባባይ በከንቱ ሲያጠፋ ምን ላድርግ ብለህ ነው..”* አሉት ይባላል።

እነሆ በዚሁ ጠሰኛ ፓለቲካ መዘዝ በሰው ሀገር የተሰደዱ ኢትዩጵያይዊያን መካከል በአብዛኛው በተሰለፉበት የሙያ ዘርፍ እጅግ የላቀ ሙያና ልምድ አካብተው፤ አድገው በያሉበት ሀገር ስማቸውና ተግባራቸው የተጠራ ወገኖቻችን ብዙ ናቸው።
አንድ ወቅት ወደ የሚወዱት ሀገራቸውና ወገናቸው ተመልሰው የበኩላቸውን ለማበርከት በህይዎት ዘመናቸው ለዚህ እንዲበቁ የሚያልሙትም አብዛኛች ናቸው። ይሁንና ይህ ህልም እውን እንዲሆን የሚያበረታታ የሚያስተማምን ሁኔታ ሳይፈጠር በምኞት ብቻ ትውልድ ተከታትሏል።

በዚህ በተፈጠረው ክፍተት እነሆ የሀገራችን የፓለቲካ ጉዳይ ለባዕዳን የተጋለጠ ከመሆኑም በላይ ለጠባብ የጎጥ ፓለቲካና ጨካ የኖሩ ወንበዴዎች ሰተት ብለው ሥርዎ መንግሥት በመጨበጥ የሕዝባችን እጣ ፈንታ ከድጡ ወደ ማጡ ሆኗል። አሁንም ፍልሰቱ፣ጨምሯል፤ የንጹሃን ደም በከንት ይፈሳል።አገራችን በዓለም ዙሪያ በችግርና በረሃብ አስጸያፊና ዘግናኝ አዘቅት ላይ ወድቃለች።

ከዚህ በኋላ ግን የሀገራችን የፓለቲካ ሁኔታ በትችት ወይም በሌላ ምክንያት ወደ ጎን የምንተወው ጉዳይ አይሆንም። የተማረው ወይም በተለያዩ የሙያ ዘርፍ የሰለጠነው የሰው ኃይል በአግባቡ በእቅድ ተይዞ በሃገር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ የገበያና የምርታማነት ስኬቶች ጋር ለውድድር በሚበቃ መልኩ ካልተመራ ከችግርና ከረሃብ ለመውጣት አይቻልም።

ይኸንን የሚያሰተውሉ ዜጎች በሀገርም ሆነ በውጭ ትልቅ ኅሊና የሚነሳ ጉዳይ ሆኗል። ለዚህም ነው በግል ሙያቸውና ኅይዎታቸው የሚያስፍልጋቸውን የቁሳዊ ፍላጎት መሟላቱ ብቻ መንፈሳይና ሞራላዊ ነጻነት ሊሰጥ አይችልም።

የወገናችን ሰቆቃ፤ሃዘን፤ በትዝብት ልናስተውለው አንችልምም።ለዚህም ነው ዛሬ ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጠው ለሀገራቸውና ለህዝባቸው ዘለቄታዊ ለውጥና መፍትሄ ለማምጣት በዓለም ስመ ጥር ኢትዮጵያዊ ባለሙያዎች፤ ምሁራኖች ሀገርና ህዝብ ወዳዶች ቆርጠው በመነሣት እንደ ቅንጅት ዓይነት የፓለቲካ ፓርቲ የመሰተረቱት፣

ዛሬ በ እስር ቤት የሚገኙት የቅንጅት መሪዎች።የሞያ ብቃትና ችሎታ፣ የፓለቲካ ራዕይ እውነተኛና ፍጹም ወገናዊነታቸው የሐገራችንን የተፈሮ ሀብት፤ የሰው ኃይል በብቃት ከቴክኖሎጂ ጋር አዛምደው በማልማት ስሙ በልመናና በችግር የጎደፈውን የአደፈውን  የአበሻ ሕዝብ ራሱን በማስቻል እንደገና ክብሩን የሚያላብሱ ስሙን የሚያድሱ ስለመሆናቸው አያጠራጥርም።

ይኸም ሲባል በአንድ ጊዜ ድንጋይ ዳቦ ያደራሉ ከሚል አነጋገር ሳይሆን የ እውነተኛ ጥረት መሰረት ጥሎ በዚህ ትውልድ ድንቅ ጅምር ሆኖ በተተኪው ትውልድ እየሰፋ የሚሄድ ትክክለኛ አቅጣጫ ጥርጊያ መንገድ ስለሚሆን ነው።

ለዚህም ደግሞ የ'ቅንጅት' ፓርቲ አቅፎ በያዛቸው ባለሙያዎች የላቀ ደርጃና መጠን ለሕዝብ ካላቸው ወደር የሌለው ፍቅር በፓለቲካ አሰላለፋቸው እንኳንስ በአፍርቃ በምዕራባዊያንም የሚተካከላቸው የለም።

ይኸንን የተገነዘቡ በችግራችን ስም፤ በምጽዋዕት ሰበብ ሰላይ፣ሚሽነር እየላኩ ባንዳ እየቀጠሩ እያነገሱ ሁሌ አንገታችንን እንድንደፋ ሰሚፈልጉ ባእዳኖች ሁሌ እንድናመልካቸው የሚፈልጉ ሁሉ በሀገራቸው ያለውን የተፈጥሮ ሃብት ሟጠው ጨርሰው ዛሬ በየሰበቡ የየሀገሩ ነዳጅና የከርሰ ምድር ሃብት ለማካበት ሲሉ በጦር ሳይቀር እየወረሩ ለዝርፊያ የሚራኮቱበት ዘመን ላይ እንገኛለን።
እንደ ኢትዩጵያ ያሉ ድሃ ሀገሮች የሚያመርቱን፤ የሚሸጡትን መጠን ጥራት ዋጋ በአለም ገበይ በከፍተኛ የቁጥጥር ማነቆ አስገብተው ቁማርና መሰናክል ሲጫወቱብን፣ የእነሱን ሸቀጥና ውራጅ ግን ሁሌ እንድናጣራ በውስጥ አስተዳደራችን፤ መንግስታችን መዋቅራችን እጃቸውን በማስገባት በቀጥታም ሆነ በተዋዋሪ ያሰገድዱናል።

በሌላ በኩል ሀገራችን ኢትዩጵያ ከርሰ ምድሯ፤ማዕድኗ ገና ያልተነካች ድንግል መሆኗን ያውቃሉና እጃቸውን አስገብተው መዝረፍ ይፈልጋሉ።
ለዚህም አቅፈው ደግፈው ለስልጣን ያበቁት የወያኔ መንግሥት ይኸንን ተግባራቸውን እንዲያከናዉኑ እጅ ነስቶ አመቻችቶላቸዋል። ለዚህም ነው አንዳንዴ ሸንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱለትና ዕድሜውን ለማራዘም ሲወጡ ሲውርዱ የሚታዩት።

የህዝባችን ሰቆቃና የሰብአዊ መብት ረገጣ ፓለቲካ ግን ከጥቅማቸው አንጻር ሚዛን የሚያነሳ ጉዳይ አይደለም።

ስለዚይም ነው በያለንበት ሀገር እየተባበርን እየተረዳዳን ይኸንን ሰይጣናዊ ሴራ ማጋለልጥና መዋጋት የሚጠበቅብን።
ትግላችን በሀገራችን ዘለቄታዊና ሁለንተናዊ መፍትሄ ለማምጣት ተነስተው በአረመኔው ወያኔ ወህኒ ቤት ታጉረው የሚሰቃዩት እውነተኛ የሕዝብ መሪዎች እስኪፈቱና ከዚያም የተነሱለት የተቀደሰ ሕዝባዊ ዓላማ መሳካት የምንችለውን ሁሉ ለማበርከት በረኸሙ አልመን መነሳት የሚገባን።

የኛ ብርታትና አንድነት የጠላቶቻችንን ዕድሜ ያስጥረዋል። በሀገር ውስጥ በየአቅጣጫው በሥራ በትግልና በለውጥ የእድገት እንቅስቃሴ ላይ የተጠመዱትን ወገኖቻችን ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግ አለብን።

በመጨረሻ ጊዜ ለውጥ የሚመጣውና የለውጡም ባለቤት መሆን ያለበት ኢትዮጵያዊያን ስለሆን በራሳችን ጉዳይ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን አለብን።

## 5) ይድረስ በእሥራት ላይ ለምትገኙ የቅንጅት መሪዎች፣ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና ለእውነት በመቆማችሁ ዘብጥያ ለወረዳችሁ ጋዜጠኞች ጭምር፡

እናንተ ታላቅ የሕዝብ መሪዎች፣ የእውነትና የእውቀት ቀንዲል የሆናችሁ በአረመኔው የወያኔ ቡድን የሚፈጸምባችሁ እስራትና እንግልት ሰፊውን ወገናቹህን ከመጠን በላይ አስቆጥቷል።

ይሁንና የምታሳዩት ፍጹም የሆነ የናንተ ዓላማ ጽናትና የመንፈስ ጥንካሬ ለመረጣችሁ ሕዝብ ትግሉን በስልት የበለጠ እንዲያጠናክር እጅግ አበርታቶታል።

የሁላችሁም የኀይዎት ታሪክ፣ የሥራ አስተውጽዖ፣ የሞያ ብቃት ጋር በጥቅሉ የመሠረታችሁት የቅንጅት ፓርቲ ራዕይ በአመራሩ የታቀፋችሁት የእውቀትና የሥራ ልምዳችሁ ጋር ሲዋሃድ እንኳንስ በአህጉራችን አፍራቃ ቀርቶ በምዕራባዊያን የሚስተካከላቹ አይገኝም።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት በጨለማው በሥቃይ ሲዳክር አይታችሁ ቀርጣችሁ በመነሳት የነጻነት ብርሃን ፈንጥቅችሁለታል፡ ውጋገኑ ከአገራችን ድንበር አልፎ በስደት ለምንገኝ ሁሉ አብርቷል።

ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ሌላ ምንም አማራጭ የለውም፣በመረጠው መሪና ፓርቲ ከመተዳደር በስተቀር፡፤
ለጊዜው የጋረደው ጭጋግ ከዳር እስከ ዳር መርጧቹህ በተነሳው ወገናችሁ የተያያዘ የትግል ቃጠሎ ብዙ ሳይቆይ ጎህ ይቀዳል።

እናንተ ለእሥር ከበቃችሁበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ነገር ተፈጽሟል፡ ወያኔው ማንነቱን አረጋግጧል። ከፋሽስት ወራሪ ጣሊያን የማያንስ በደል ፈጽሟል፡ ወገናችሁ በታሪኩ ለጠላት ዓለም ያወቀለት ጀግንነት ቢኖረውም የአሁኖቹ ከውስጡ የተወሳሰቡና ራሱን መስለው የተመረዙ ስለሆኑ እጅግ ታግሶ በረቀቀ ብልሃት ሊረታችሁው ከልቡ ቆርጧል።

በዚህ ፈታኝ ወቅት የባንዳዎችና የሆዳም ከሃዲዎች ጋጋታ ነገ በትውልድና በታሪክ ፊት ማፈሪያና መሣቂያ ከመሆን በስተቀር ትግሉን ፍጹም አይገቱትም።

ትግሉ በሁለንተናዊ ዘርፉ በሀገር ውስጥና ውጭም ቀጥሏል።

እስከዚያው እናንተ ብርቅዬ የሆናችሁ ወንድሞች፤እህቶቹና መሪዎቹ በጤናችሁ ነቅታችሁ እንድትቆዩ ዘዎትር በጸሎት ይስቧችኋል።

ወገናቹህ ወሳኝ ድሉን በወሳኝ ትግሉ በቅርቡ ይቀዳጃል።
አምላካችን ለሁላችሁም የመንፈስና የአካል ጥንካሬ ይስጣችሁ። አሜን!

*“የጎንቻው”* yegonchaw@yahoo.co.uk